አፍለሰ፡ናቡዛርዳን፡ሊቀ፡መበስላን፡ነፍሰ፡
አይሁድ፡
የአዛገሮች ፡ አለቃ ፡ ናቡዛርዳን ፡ የአይ
ሁድን፡ወገኖች፡ማረከ፤

፳፡፻፡፴ወ፳፡፡
የተማረኩትም ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡
አምስት፡ናቸው፤

ወኵሉ፡ነፍስ፡፴፻ወ፮፻፡
መላው፡አራት፡ሺህ፡ከስድስት፡መቶ፡
ናቸው፤

፴፩፤ ወኮነ ፡ በ፴ወ፯፡ ዓመት ፡ እምዘ
ፈለሰ፡ኢኮንያን፡ንጉሠ፡ይሁዳ፡
የይሁዳው፡ንጉሥ፡ኢኮንያን፡በነገሠ፡
በሠላሳ ፡ ስድስት ፡ ዘመን ፡ እንዲህ ፡
ሆነ፤ ሠላሳ፡ ወስድስቱ፡ ያለው፡ ናቡከ
ደነፆር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የሆነበት ፡
ሀያ፡ አምስት ፡ ዘመን ፡ የሴዴቅያስ ፡
አሥራ፡ አንድ፡ ይህንን፡ ቢገጥሙት፡
(ቢደምሩት)፡ ሠላሳ፡ ስድስት፡ ያለው፡
ይህንን፡ ነው፤ ሠላሳ ወ፯ቱ፡ ቢል፡ የዮ
ልማሮዴቅ፡ተጀምሯልና፤

በ፲ወ፪ቱ፡ወርኅ፡
በአሥራ ፡ ሁለተኛው ፡ ወር ፡
በመጋቢት፡

አመ፡፳ወ፭፡ለሠርቅ፡
መጋቢት፡በባተ፡በሀያ፡አምስተኛው፡
ቀን፤

ነሥአ ፡ ኢዮልማሮዴቅ ፡ ንጉሠ ፡ ባቢሎን
በዓመተ ፡ መንግሥቱ ፡ ለኢኮንያን ፡ ንጉሠ ፡
ይሁዳ፡
ኢዮልማሮዴቅ ፡ በነገሠ ፡ በመጀመ
ሪያው፡ዘመን፡የይሁዳው፡ንጉሥ፡ኢኮ
ንያንን፡አመጣው፤ናቡከደነፆር፡ሰባት፡
ዓመት፡እሪያ፡ሆኖ፡ኖረ፤ሆኖ፡ሳለ፡
ብትልም፡ኢዮልማሮዴቅ፡ምስለኔ፡

ሁኖ፡ሲገዛ፡ኖረ፤ከተመለሰ፡በኋላ፡
እንግዲህ፡ወዲህ፡መንግሥት፡ቀም
ሷልና፡መንግሥት፡ያፋልሳል፡ብሎ፡
ብትልም፡ያውከኛል፡ብሎ፡አሥሮት፡
ሳለ፡ኢኮንያንን፡ያጫውተው፡ነበር፤
ፈጣሪያችንን ፡ በድለን ፡ ቀረብን ፡
እንጂ፡መንግሥት፡ክህነት፡ሰጥቶን፡
ነበር ፡ እያለ ፡ ኋላ ፡ ሲነግሥ ፡
ለሥልጣን፡አብቅቶታል፤

ወአውጽአ፡እምቤተ፡ሞቅሕ፡
ከግዞት፡ቤት፡አወጣው፤

፴፪፤ ወተናገሮ፡ሠናየ፡
በጎ፡ነገር፡ተናገረው፤

ወረሰየ ፡ መንበሮ ፡ መልዕልተ ፡ መንበረ ፡
መንግሥት፡እለ፡ምስሌሁ፡
ዙፋኑንም ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡
ከሚቀመጡ፡ ነገሥታት ፡ ዙፋን ፡
በላይ፡አደረገው፤

፴፫፤ ወወለጠ፡ልብሰ፡ተሞቅሖቱ፡
የግዞት፡ቤት፡ልብሱን፡ለወጠለት፤

ወበልዓ፡በቅድሜሁ፡ኅብስተ፡ዘልፈ፡በኵሉ
መዋዕለ፡ሕይወቱ፡
ባለ፡በዘመኑ፡ሁሉ፡ዘወትር፡በፊቱ፡
ግብር፡ይበላ፡ነበር፤

፴፬፤ ወፈተቶ፡ሎቱ፡ፍተ፡ዘዘልፍ፡
የዘወትር፡ድርጎ፡ዳረገው፤

ወተውህበ፡ሎቱ፡እምኀበ፡ንጉሠ፡ባቢሎን፡
እንተ፡ጸብሐት፡
እየነጋ፡እየመሸ፡ከባቢሎን፡ንጉሥ፡
ድርጎ፡ተሰጠው፤

እስከ፡እለ፡ሞቱ፡በኵሉ፡መዋዕለ፡ሕይወቱ፤
ባለ ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ እስኪሞት ፡
ድረስ፡ድርጎ፡ተሰጠው፤

ተፈጸመ፡ዘኤርምያስ፡ነቢይ።



# መጽሐፈ ፡ ባሮክ ፤

## ምዕራፍ ፡ ፩ ፤

### ጉባዔ፤

፩፤ ዝንቱ ፡ ነገረ ፡ መጽሐፍ ፡ ዘጸሐፈ ፡
ባሮክ፡ወልደ፡ኔርዩ፡
የኔርዩ ፡ ልጅ ፡ ባሮክ ፡ የጻፈው ፡
የመጽሐፍ፡ነገር፡ይህ፡ነው፤

ወልደ፡ማሴው፡
ኔርዩን፡የማሴው፡ልጅ፡አለው፤

ወልደ፡ሴዴቅዩ፡
ማሴውን፡የሴዴቅዩ፡ልጅ፡አለው፤

ወልደ፡ኬልቅዩ፡
ሴዴቅዩን፡የኬልቅዩ፡ልጅ፡አለው፤

ባቢሎን፤
ወደ፡ባቢሎን፡የመጣ፡የኔርዩ፡ልጅ
ባሮክ፡የጻፈው፡የመጽሐፍ፡ነገር፡
ይህ፡ነው፤

፪፤ በኃምስ፡ዓመት፡
ሴዴቅያስ፡በነገሠ፡በአምስተኛው፡
ዘመን ፤ አንድም ፡ ወተቀንየ ፡
ኤልያቄም፡ሠለስተ፡ዓመተ፡ይላልና፡
ከኤልያቄም፡ሁለት፡ዓመት፤ የሴዴ
ቅያስ ፡ ሦስት ፡ አምስት ፡ ያለው ፡
ይህንን፡ነው፤

በሰቡዓ፡ሠርክ፡
ሠርቀ፡ወርኅ፡በባተ፡በሰባተኛው፡
ቀን፡ያልታወቀ፡ወርኅ፡ነው፤

አመ፡ነሥእዋ፡ፋርስ፡ለኢየሩሳሌም፡
ከመ፡ነሥእዋ፡ሲል፡ነው፤የፋርስ፡
ሰዎች፡ኢየሩሳሌምን፡እንዲማርኳት፤

ወአውዓይዋ፡በእሳት፡
በእሳትም፡እንዲያቃጥሏት፤አንድም፡
እምድኅረ፡ቢል፡የፋርስ፡ሰዎች፡ኢየ
ሩሳሌምን፡ከማረኳት፡በኋላ፡ወአው
አይዋ፡በእሳትም፡ካቃጠልዋት፡
በኋላ፡ በኢኮንያን፡ጊዜ፤አንድም፡
እምቅድመ፡ይንሥእዋ፡ቢል፡የፋርስ፡
ሰዎች፡ኢየሩሳሌምን፡ሳይማርኳት፡
በእሳትም፡ሳያቃጥሏት፡በሴዴቅያስ፡
ጊዜ፡የመጣ፡የመጽሐፍ፡ነገር፡ይህ፡
ነው፤

፫፤ወአንበበ ፡ ባሮክ ፡ ዘ ፡ መጽሐፈ ፡
ዘተጽሕፈ፡
ባሮክ፡የተጻፈውን፡ይህን፡መጽሐፍ፡
አነበበ፤ ጸሐፊ ፡ የጻፈውን ፡ የጐደ
ለውን፡ ለመምላት ፡ የጠመመውን ፡
ለማቅናት ፡ መልሶ ፡ እንዲያነብብ ፡
አነበበ፤

ኀበ፡ኢኮንያን፡ወልደ፡ኢዮአቄም፡ንጉሠ፡
ይሁዳ፡
ወደ ፡ ይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡
ኢዮአቄም፡ልጅ፡ወደ፡ኢኮንያን፡
የሚሰደውን፤አንድም፡እርሱ፡የሚል
ከውን፤

ወኵሉ፡ሕዝብ፡ዘመጽአ፡
ወደ፡ሕዝቡ፡ሁሉ፡የሚሰደውን፤

፬፤ ወለአከ፡ኢየሩሳሌም፡ኀበ፡ካህናት፡
በኢየሩሳሌም፡ወደ፡አሉ፡ካህናትም፡
የሚልከውን፡አነበበ፤አንድም፡ኀበ፡
ኢኮንያን፤ከይሁዳው፡ንጉሥ፡ከኢዮ
አቄም፡ልጅ፡ከኢኮንያን፡ዘንድ፡
የመጣውን፤ ወኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ከሕ
ዝቡም፡ዘንድ፡የመጣውን፡ወለአከ፡
ኢየሩሳሌም፤በኢየሩሳሌም፡ካሉ፡ከካ
ህናቱም፡ዘንድ፡የሚልከውን፡ይህን፡
መጽሐፍ፡አነበበ፤

www.ethiopianorthodox.org

አመ ፡ ነሥኡ ፡ ንዋየ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምቤተ፡መቅደስ፤
የቤተ ፡ እግዚአብሔሩን ፡ ንዋየ ቅድሳት ፡ ከቤተ ፡ መቅደስ ፡ ማርከው ፡ በወሰዱ ፡ ጊዜ ፡ የተጻፈውን ፡ ይህን፡ መጽሐፍ፡አነበበ፤

፰፤ወገብረ፡ሴዴቅያስ፡ንዋየ፡ብሩር፤
በመካከል ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አገባበት ፡ ሴዴቅያስ ፡ የብር ፡ ዕቃ ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳት፡አሠርቶ፤

እምድኅረ ፡ አፍለሶ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ንጉሠ ፡ ባቢሎን፡ለኢኮንያን፤
የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ኢኮንያንን፡ከማረከው፡በኋላ፤

ወለሕዝበ ፡ ምድር ፡ እምኢየሩሳሌም ፡ ወሰዶሙ፡ባቢሎን፤
ሕዝቡንም ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወደባቢሎን ፡ ማርኮ ፡ ከወሰዳቸው ፡ በኋላ ፡ የብሩን፡ዕቃ፡አሠርቶ፤

ወፈነወ፡ሎሙ፡ወርቀ፡
ከወርቁ፡ጋራ፡አሲዞ፡ሰደደላቸው፤

፲፩፤ ወይቤ፡ጸልዩ፡በእንተ፡ሕይወተ፡ናቡከደነፆር፡ንጉሠ፡ባቢሎን፡
የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆርን ፡ በሕይወት፡ያኑረው፡ብላችሁ፡ለምኑ፤

ወበእንተ፡ሕይወተ፡ብልጣሶር፡ወልዱ፤
ልጁ ፡ ብልጣሶርንም ፡ በሕይወት ፡ ያኑረው፡ብላችሁ፡ለምኑ፤

ከመ፡ይኩን፡መዋዕሊሆሙ፡ከመ፡መዋዕለ፡ ሰማይ፡ዲበ፡ምድር፤
ዘመናቸው ፡ ሰማይ ፡ በአድማስ ፡ ላይ ፡ ጸንቶ ፡ የኖረውን ፡ ዘመን ፡ ያህል ፡ ይኖር፡ዘንድ፡ለምኑ፤

፲፪፤ ወጸልዩ ፡ ለነሂ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡
ለኛም ፡ ከፈጣሪያችን ፡ ከእግዚአብሔር፡ዘንድ፡ለምኑልን፤

እስመ፡አበስነ፡ለእግዚአብሔር፡አምላክነ፤
ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔርን ፡ በድለናልና፤

፲፬፤ወአንብብዋ፡ለዛቲ፡መጽሐፍ፡በቤተ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ትካት ፡ ያነብብዋ፤ ለዳግም፡ሕግ፡ካህናት፡በዕለተ፡በዓል፡
ቀድሞ ፡ ካህናቱ ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር፡ዳግም፡ሕግን፡ያነብቧት፡እንደነበረ፡ይህቺን፡መጽሐፍ፡በበዓል፡ ቀን ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንብቧት ፤ አንድም ፡ ለኤርምያስ ፡ የላከኋትን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ቀድሞ ፡ እነኢኮንያን፡በኢየሩሳሌም፡ሳሉ፡ያከብሩት፡በነበረ፡በበዓል፡ቀን፡በቤተ፡እግዚአብሔር፡አንብቧት፤

፲፭፤ ወበሉ ፡ ጽድቅ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክነ፡
የፈጣሪያችን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቸርነቱን፡ተናገሩ፤

ወለነሰ ፡ ኀፍረት ፡ ለገጽነ ፡ ለሰብአ ፡ ይሁዳ፡ ወለኢየሩሳሌም፤
የይሁዳና ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ሰዎች ፡ የእኛን ፡ ፊት ፡ ግን ፡ ኃፍረት ፡ ኮሰቍልና፡ሸፈነን፤

ወለነገሥትነ፡ወለመሳፍንቲነ፤
የነገሥታቱንና፡የመሳፍንቱን፤

ወለካህናቲነ፡ወለነቢያቲነ፤
የካህናቱንና የመምህራኑን ፡ ፊት ፡ ኃፍረት፡ጕስቍልና፡ሸፈነው፤

፲፰፤ ወኢሰማዕነ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ፡
የፈጣሪያ...



ወኢሖርነ ፡ በትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ፡ዘወሀበነ፡
በሠራልን ፡ በፈጣሪያችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ጸንተን ፡ አልኖርንም፤

፲፱፤ እምአመ ፡ አውጽአሙ ፡ ለአበዊነ ፡ እምድረ፡ግብፅ፡እስከ፡ዛ፡ዕለት፡
አባቶቻችንን፡ከግብፅ፡ከአወጣቸው፡ ጀምሮ ፡ እስከዚች ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ በሠራልን ፡ በፈጣሪያችን ፡ ሕግ ፡ ጸንተን፡አልኖርም፤ሲጽፍ፡እስከ፡ዛ፡ ዕለት ፡ ይላል፤ አለውናሁ ፡ ማንሻ ፡ አንድም፡አባቶቻችንን፡ከግብፅ፡ከአወጣቸው፡ጀምሮ፡እስከዚች፡ቀን፡ ድረስ፤

አለውናሁ፡ለእግዚአብሔር፡አምላክነ፡
ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔርን ፡ በደልነው፡ካድነው፤

፳፤ ወረከበነ፡ዝ፡መርገም፡እኩይ፡
ይህ፡ክፉ፡መርገም፡አገኘን፡ማለት፡ ክፉ፡መከራ፡ደረሰብን፤

እስመ ፡ ሖርነ ፡ ወተቀነይነ ፡ ለአማልክተ ፡ ነኪር፡
ሔደን፡ለአሕዛብ፡ጣዖታት፡ተገዝተናልና ፤ አንድም ፡ ለአማልክት ፡ ነኪራን፡ቢል፡ልዩ፡ለሆኑ፡ጣዖታት፡ ተገዝተናልና፤

ወበጽሐነ፡ዘጽሑፍ፡ውስተ፡ኦሪተ፡ሙሴ፡
በሙሴ ፡ የተጻፈው ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ደረሰብን።

## ምዕራፍ፡፪፡

፩፤ ወበልዓ ፡ ሰብእ ፡ ሥጋ ፡ ደቂቁ ፡ ወአዋ...
በው ፡ የወንዶች ፡ ልጆቹን ፡ የሴቶች ፡

ቸውን፡በላ፤

፬፤ ወዘረወነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውስተ ፡ አሕዛብ፡ዘዓውድነ፡
እግዚአብሔር ፡ በዙሪያችን ፡ ወደ ፡ አሉ፡አሕዛብ፡በተነን፤

ወኢተጋነይነ፡ለእግዚአብሔር፡
ለእግዚአብሔር፡አልተገዛንም፤

ወኢሐደገነ፡እከየ፡ልብነ፡
የልቡናችን ፡ ክፋት ፡ አልተወንም ፡ አንድም፡ወኢሐደግነ፡እከየ፡ልብነ፡ የልቡናችንን፡ክፋት፡አልተውንም፡ አንድም ፡ ወኢሐደገ ፡ እከየ ፡ ልብነ ፡ ሳታናብብ ፡ ልባችን ፡ ክፋትን ፡ አልተወም፤

፲፩፤ ወይእዜኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ እስራኤል፡
አሁንም፡የእስራኤል፡ፈጣሪ፡እግዚአብሔር፤

ዘአውጻእከ፡ሕዝበከ፡እምድረ፡ግብፅ፡
ወገኖችህን፡ከግብፅ፡ያወጣህ፤

በእድ፡ፅንዕት፡
በጸናች፡ሥልጣን፤

ወበትእምርት፡ወበመንክር፡
በድንቅ፡ተአምራት፤

ወበኃይል፡ዓቢይ፡
በጽኑ፡ኃይል፤

ወበመዝራዕት፡ልዑል፡
ገናና፡በሆነ፡ሥልጣን፡ያወጣህ፡የእስራኤል፡ፈጣሪ፡እግዚአብሔር፤

፲፫፤ አቅርር፡መዓተከ፡እምኔነ፡
መዓትህን፡ከእኛ፡አርቅ፤

እስመ፡ኅዳጠ፡ተረፍነ፡በውስተ፡አሕዛብ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወስማዕ፡ጸሎተነ፣
ልመናችንን፡ስማ፤
ወአድኅነነ፣
ከመከራው፡አድነን፤
እስመ፡አንተ፡እግዚአብሔር፡አምላክነ፣
ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ አንተ ፡ ነህና፤

፭፣ነጸር፡እግዚእ፡እምቤተ፡መቅደስከ፣
አቤቱ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ተብለህ፡ በምትመሰገንበት ፡ በቤተ ፡ መቅደስህ፡የደረሰብንን፡መከራ፡እይ፣ ተመልከት፤

፮፣አኮ፡እለ፡ውስተ፡ሲኦል፡ዘይሴብሑከ፡
በመቃብር ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ የሚያመሰግኑህ፡አይደለም፤
ዳዕሙ ፡ ነፍስ ፡ ድኅንት ፡ ወነፍስ ፡ ርኅብት ፡ እንተ፡ፀግበት፡ተአኵተከ፡እግዚአብሔር፣
እግዚአብሔር ፡ ከሞት ፡ ከመከራ ፡ የዳነች ፡ ተርባ ፡ የጠገበች ፡ ሰውነት ፡ ታመሰግንሃለች፡እንጂ፤

፯፣ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤
አጽምዑ፡እዘኒክሙ፣
በጆሮዋችሁ፡አድምጡ፤
ወተቀነዩ፡ለንጉሠ፡ባቢሎን፣
ለባቢሎን፡ንጉሥ፡ተገዙ፤
ወትነብሩ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ እንተ ፡ ወሀብ ክዎሙ፡ለአበዊክሙ፣
እንዲህ፡ያደረጋችሁ፡እንደሆነ፡ለአባቶቻችሁ ፡ በሰጠኋቸው ፡ ሀገር ፡ ጸንታችሁ፡ትኖራላችሁ፤

፰፣ ወእመ ፡ ኢሰማዕክሙ ፡ ቃለ ፡ እግዚአ

ወኢተቀነይክሙ፡ለንጉሠ፡ባቢሎን፣
ለባቢሎን፡ንጉሥ፡ባትገዙ፤

፱፣ የሐልቅ፡እምአህጉረ፡ይሁዳ፣
ከይሁዳ፡አገሮች፤
ወእምአፍአሃኒ፡ለኢየሩሳሌም፣
ከኢየሩሳሌም፡አደባባይ፤
ቃለ፡ትፍሥሕት፡ወኃሤት፣
የተድላ፡የደስታ፡ቃል፡ይጠፋል፤
ቃለ፡መርዓዊ፡ወቃለ፡መርዓት፣
እገሌ ፡ እገሊትን ፡ ያግባ ፣ እገሊት ፡ እገሌን ፡ ታግባ ፣ የሚል ፡ ቃል ፡ ይጠፋል፤ አንድም ፡ እንደ ፡ አሠርት፡ ያለ፡እየዘፈኑ፡የሚያከብሩት፡የሠርግ፡ በዓል፡አለና፤
ወኵሉ፡ምድር፡ይከውን፡በድወ፣
አገሩ፡ሁሉ፡ምድረ፡በዳ፡ይሆናል፤

፲፣ ወኢሰማዕነ፡ቃለከ፣
ቃልህን፡አልሰማንም፤
ወኢተቀነይነ፡ለንጉሠ፡ባቢሎን፣
ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ለናቡከደነፆር ፡ አልተገዛንም፤
ወበጽሐነ ፡ ዘነበብከ ፡ በእደ ፡ አግብርቲከ ፡ ነቢያት፣
በባሮችህ ፡ በነቢያት ፡ ቃል ፡ የተናገርከው፡ነገር፡ደረሰብን፤
እንዘ፡ትብል፣
እንዲህ፡ብለህ፡በኤርምያስ፡አድረህ፡ ነገርኸን፡አልሰማንምና፡ይህ፡ሁሉ፡ መከራ፡ደረሰብን፤
ያወጽኡ፡አእፅምተ፡ነገሥት፣
የነገሥታቱን፡አጥንት፤
ወአእፅምተ፡አበ[illegible]



ርከው፡ደረሰብን፤አንድም፡ያወጽኡ፡ አእፅምተ፣የነገሥታቱን፡ወገኖችና፡ ወአእፅምተ፡ አበዊነ፡የአባቶቻችንን፡ ወገኖች፡ከሀገራቸው፡ማርከው፡ይወስ ዷቸዋል፡ብለህ፡የተናገርከው፡ነገር፡ ደረሰብን፤

፲፩፣ ወናሁ ፡ ገደፍዎሙ ፡ ውስተ ፡ ዋዕየ ፡ መዓልት፡ወቍረ፡ሌሊት፣
እነሆ ፡ በቀን ፡ ሐሩር ፡ በሌሊት ፡ ቍር ፡ ጣሏቸው፤
ወተዪወውነ፣
ተማረክነ፤
ወሞትነ፡እኩየ፡ሞተ፡
ክፉ፡አሟሟትን፡ሞትነ፤
በረኃብ፡ወበኲናት፣
በጦር፡በቀጠና፡ሞትን፤

፲፪፣ ወአእመርክዎሙ ፡ ከመ ፡ ኢይሰ ምዑኒ፣
እንዳይሰሙኝ፡አወቅኋቸው፤
እስመ፡ሕዝብ፡ጽኑዓነ፡ክሳድ፡እሙንቱ፤
ክሳደ ፡ ልቡናቸውን ፡ ያጸኑ ፡ ወገኖች ፡ ናቸውና፤

፲፫፣ ወየአምሩ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኮሙ፤
ፈጣሪያቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ሆነ፡ያውቃሉ፤
ወእሁቦሙ፡ልበ፣
የሚያስተውሉበትን፡ልቡና፤
ወእዝነ፡ለሰሚዕ፡
የሚሰሙበትን፡ጆሮ፡እሰጣቸዋለሁ፣

ወይዜከሩ፡ስምየ፡
ስሜን፡ያስባሉ፤

፲፬፣ወየኀድጉ፡እከየ፡ምግባሮሙ፤
እኩየ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ክፉ ፡ ሥራቸውን ፡ ይተዋሉ፤
ወኢይዜከሩ ፡ ፍኖተ ፡ አበዊሆሙ ፡ እለ ፡ አበሱ፡ቅድመ፡እግዚአብሔር፣
በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የበደሉ ፡ የአባ ቶቻቸውን፡ሥራ፡አያስቡም፡ማለት፡ አይበድሉም፤

፲፭፣ወአገብአሙ፡ብሔረ፡ኀበ፡መሐልኩ፡ ለአበዊሆሙ፤
ለአባቶቻቸው ፡ ወደ ፡ ማልኩላቸው ፡ አገር፡እመልሳቸዋለሁ፤
ለአብርሃም፡ወለይስሐቅ፡ወለያዕቆብ፣
ለአብርሃም ፡ ለይስሐቅ ፡ ለያዕቆብ ፡ ወደ፡ማልኩላቸው፡እመልሳቸዋለሁ፤
ወይኴንንዋ፣
ይገዟታል፤
ወአበዝኖሙ፤
አበዛቸዋለሁ፤
ወኢይውሕዱ፣
አያንሱም፤

፲፮፣ወእሠርዕ፡ሎሙ፡ሥርዓተ፡ዘለዓለም፣
ለዘላለም ፡ ጸንታ ፡ የምትኖር ፡ ሥርዓትን፡እሠራላቸዋለሁ፤
ከመ፡እኩኖሙ፡አምላኮሙ፤
የፍቅር ፡ የሃይማኖት ፡ አባት ፡ እሆ ናቸው፡ዘንድ፤
ወእሙንቱኒ ፡ ይከውኑኒ ፡ ሕዝብየ ፡
እነርሱም፡ የፍቅር ፡ የሃይማኖት ፡ [illegible]፡ይሆኑኛል፣

www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ወገኖቼ ፡ እስራ ኤልን፡ከሰጠኋቸው፡ከሀገራቸው፡አላ ስማርካቸውም።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ፡

### ጉባዔ፤

፩፤ እግዚእ ፡ ዘትነግሥ ፡ አምላከ ፡ እስራኤል፤

ነግሠህ ፡ የምትኖር ፡ የእስራኤል ፡ ፈጣሪ፡አቤቱ፤

ነፍስ፡ርኅብት፡ወነፍስ፡ትክዝት፡ጸርሐት፡ ኀቤከ፤

የተራበች፡ያዘነች፡ሰውነት፡ከአንተ፡ ዘንድ፡ጮኸች፤

፪፤ ስማዕ፡እግዚእ፡ወተሠሃላ፤

አቤቱ፡ሰምተህ፡ይቅር፡በላት፤

እስመ፡አበስነ፡ቅድሜከ፤

በፊትህ፡በድለናልና፡ማለት፡አንተን፡ በድለናልና፤

፫፤ እስመ፡አንተ፡ዘትነብር፡ለዓለም፤

ለዘለዓለም ፡ ጸንተህ ፡ የምትኖር ፡ አንተ፡ነህና፤

ወንሕነሰ፡ንትኀጐል፡ለዝሉፉ፤

እኛ፡ግን፡ለዘለዓለሙ፡ፈጽመን፡እን ጠፋለን፤

፬፤ እግዚእ፡ዘትነግሥ፡ለኵሉ፡አምላከ፡ እስራኤል፤

ለሁሉ ፡ ነግሠህ ፡ የምትኖር ፡ የእስ ራኤል፡ፈጣሪ፡አቤቱ፤

ስማዕ፡ጸሎተ፡ምውታን፡እስራኤል፤

የምውታን ፡ ልቡና ፡ የእስራኤልን ፡ ልመና፡ስማ፤

ወደቂቅ፡እለ፡ጌገዩ፡በቅድሜከ፤

ወኢሰምዑ፡ቃለከ፤

ቃልህን፡ያልሰሙ፤

፭፤ወተለውነ፡እኩየ፤

ክፉ፡ነገርን፡የተከተልነ፡የእኛንም፡ ልመና፡ስማ፤

ወኢተዘከርነ፡ኃጢአተ፡አበዊነ፤

የአባቶቻችንንም ፡ ኃጢአት ፡ አላሰ ብንም፤

ተዘከር፡እዴከ፡ወስመከ፡በዝ፡መዋዕል፤

በዚህ፡ዘመን፡ሥልጣንህን፡መሐሪ፡ ወመስተሣህል፡መሆንህን፡አስብ፤

፮፤ እስመ ፡ አንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ፤

ፈጣሪያችን፡እግዚአብሔር፡አንተ፡ ነህና፤

ወንሴብሐከ፡እግዚእ፤

አቤቱ፡እናመሰግንሃለን፤

፯፤ እስመ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ወደይከ ፡ ፍርሃተ፡ውስተ፡ልብነ፤

ስለዚህ ፡ ነገር ፡ አንተን ፡ መፍራት ፡ አንተን፡ማምለክ፡በልቡናችን፡አሳድ ረህብናልና፤

ከመ፡ንጸውዕ፡ስመከ፤

ስምህን፡እንጠራ፡ዘንድ፤

ወንሰብሕከ፡በኀበ፡አፍለሱነ፤

ማርከው ፡ በወሰዱን ፡ ሀገር ፡ እናመሰ ግንህ፡ዘንድ፤

፰፤ስማዕ፡እስራኤል፡ትእዛዘ፡ሕይወት፤

ስማዕና ፡ ስማዕ ፡ አንድ ፡ ወገን ፤ አን ድም፡የላይኛው፡ስማዕ፡ቃሉ፡የባሮክ፡ ነው ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በባቢሎን ፡ ላሉ፡ ሰጥቶ ፡ የ[illegible]



ወአጽምዕ፡ምክረ፡ጥበብ፤

የጥበብ፡ምክርን፡ስማ፤

፱፤ምንት፡ውእቱ፡እስራኤል፤

እስራኤል፡ምድር፡ነው፤ሕዝበ፡እግዚ አብሔር፡አልነበረም?

ወለምንት፡ውስተ፡ብሔረ፡ፀር፡ሀሎ፤

በጠላቱስ፡ሀገር፡የሚኖር፡በኃጢአቱ፡ አይደለም፤

፲፤ወበልየ፡በብሔረ፡ነኪር፤

በባዕድ፡አገር፡ጠፋ፤

ወረኵሰ፡ምስለ፡አብድንት፤

እንደ፡ሬሣዎች፡ጐሰቈለ፤

ወተኈለቈ፡ምስለ፡እለ፡ውስተ፡ሲኦል፤

ሙተው ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ከወረዱ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ተቈጠረ ፡ (ለምን ፡ ተቈጠረ፡ብትልም)፤

፲፩፤ወኀደገ፡ነቅዓ፡ሕይወት፤

የሕይወት፡መገኛ፡ሕግን፡ተወ፤

፲፪፤ሶበሰ፡ሖርከ፡በፍኖተ፡እግዚአብሔር፤

በእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ ጸንተህ ፡ ብትኖር፤

እምነበርከ፡በሰላም፡ለዓለም፤

ለዘለዓለሙ ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ በኖርክ፡ነበር፤

፲፫፤ተመሀር፤

ተማር፤

አይቴ፡ውእቱ፡ጥበብ፤

ጥበብ፡መገኛው፡ወዴት፡ነው፤

ወአይቴ፡ውእቱ፡ኃይል፤

ኃይልስ፡መገኛው፡ወዴት፡ነው፤

[illegible]

ዕውቀትስ፡መገኛው፡ወዴት፡ነው፤

ወአይቴ፡ውእቱ፡ሐይው፡ለነዋህ፡መዋዕል፤

ብዙ ፡ ዘመን ፡ መኖር ፡ መገኛው ፡ ወዴት፡ነው፤

ወአይቴ፡ውእቱ፡ብርሃነ፡አዕይንት፤

የዓይኖችስ ፡ ብርሃን ፡ መገኛው ፡ ወዴት፡ነው፤

፲፬፤ወለጥበብ፡መኑ፡ረከበ፡ብሔራ፤

የጥበብ፡ሀገሯን፡ያወቀ፡ማነው፤

ወመኑ፡ቦአ፡ውስተ፡መዛግብቲሃ፤

ምሥጢሯን፡የመረመረ፡ማነው፤

፲፭፤ ወአይቴ ፡ እሙንቱ ፡ መላእክተ፡ አሕዛብ፤

የአሕዛብ፡አለቆች፡ወዴት፡ናቸው፡ ወዴት፡አሉ፤

እለ፡ቀነይዎሙ፡ለአራዊተ፡ገዳም፤

ለማዳ፡አራዊትን፡የገዙዋቸው፤

ወተዋነይዎሙ፡ለአዕዋፈ፡ሰማይ፤

በአዕዋፍ፡የተጫወቱባቸው፤

፲፮፤ሐልቁ፡ወወረዱ፡ውስተ፡ሲኦል፤

እነርሱስ፡ሙተው፡ወደ፡መቃብር፡ ወረዱ፤

ወተንሥኡ፡ህየንቴሆሙ፡ካልአን፤

ስለ፡እነርሱ፡ፈንታ፡ሌሎች፡ትሩፋን፡ ተነሡ፤

፲፯፤ወርእዩ፡ብርሃነ፡ንዑሳን፤

ትሩፋን፡ብርሃነ፡ረድኤቱን፡አዩ፤

ወነበሩ፡ውስተ፡ምድሮሙ፤

በሀገራቸው፡ተዘልለው፡ኖሩ፤

[illegible]ጥበብሰ፡ኢያእመሩ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፰፤ ወአሠሮሂ፡ኢረከቡ፤
ኢታመልክንም : አላወቁም ፤ ኢታመ
ልክን : አሠር : አላት : ፍለጋ : ከሀገር :
ከመንደር : እንዲያደርስ : ኢታም
ልክም : ከዘጠኙ : ሕግጋት : ታደርሳ
ለችና፤

ወኢተወከፍዋ፡ደቂቆሙ፤
ልጆቻቸውም፡አልተቀበሏትም፤

ወርኅቁ፡እምፍኖቶሙ፤
ከሕጋቸው፡ከዘጠኙ፡ቃላት፡ራቁ፤

፲፱፤ ወኢሰምዑ፡ከነዓን፤
እስራኤል : ሕግ : ጠበቁ : ሲሉ :
የከነዓን : ሰዎች : አልሰሙም ፤ አን
ድም፡ሕግ፡ያፈረሱ፡እስራኤል፡ብቻ፡
አይደሉም ፤ የከነዓን : ሰዎችም :
አልሰሙም፤

ወኢርእዩ፡ቴምና፤
እስራኤል : ሕግ : ጠበቁ : ሲሉ :
የቴምና፡ ሰዎች : አልሰሙም ፤
አንድም፡ ሕግ : ያፈረሱ : እስራኤል :
ብቻ : አይደሉም ፤ የቴምና : ሰዎችም :
አልሰሙም፤

፳፤ ወደቂቀ : አጋር : እለ : ኀሠሥዋ :
ለጥበብ፡ኅበ፡ምድረ፡እስራኤል፤
በእስራኤል : ዕፃ : ጥበብን : የሚፈ
ልጓት : የአጋር : ልጆችም : አል
ሰሙም፤

፳፩፤ ወእፎ : ዓቢይ : ቤተ : እግዚአ
ብሔር፡ወነዋህ፤
የእግዚአብሔር : ማደሪያ : ቤተ :
መቅደስ፡እንዴት፡ሰፊ፡ደግ፡ነበር፤

አልቦ፡ማኅለቅት፡ላዕሌሁ፤
ከእርሱ : ለሚገኘው : ተድላ : ደስታ :
ፍጻሜ፡የለውም፤

ወአልቦ፡መሥፈርት፤
ሥፍር፡ቁጥርም፡የለውም፤

፳፪፤ መኑ፡ዘዓርገ፡ሰማየ፤
ወደ፡ሰማይ፡ወጥቶ፤

ወነሥአ፤
ሕግን፡የተቀበላት፡ማነው?

ወአውረዳ፡እምነ፡ደመናት፤
ከደመናት፡ያወረዳት፡ማነው?

፳፫፤ መኑ፡ዐደወ፡ባሕረ፡ወረከባ፤
ባሕሩን : ተሻግሮ : ሒዶ : ያገኘትስ፤
ማነው?ማለት፡ያወቃት፤

ወአምጽአ፡በወርቅ፡ቀይሕ፤
በወርቅ : ገዝቶ : ያመጣት : ማነው?
አንድም : ከደመናት : ያወረዳት ፤
በቀይ፡ወርቅ፡ገዝቶ፡ያመጣት፡የለም፤

፳፬፤ አልቦ፡ዘየአምር፡ፍኖታ፤
ሥራዋን፡የሚያውቅ፡የለም፡ማለት፤
ዘጠኙን፡ሕግጋት፡የሚያውቅ፡የለም፤

ወዘይሔልዮ፡ለአሠራ፤
ፍለጋዋንም : የሚያስበው : የለም ፤
ማለት፡ኢታምልክን፡የሚያውቀው፤
የለም፤

፳፭፤ ዘኵሎ፡የአምር፡የአምራ፤
ሁሉን፡የሚያውቅ፡ጌታ፡ያውቃታል፤
እንጂ፤

ወረከባ፡በጥበቡ፡ዘፈጠራ፡ለምድር፤
በባሕርይ : ጥበቡ : ምድርን : የፈ
ጠራት፡እርሱ፡ያውቃታል፡እንጂ፤

ወለዓለም፤
ለዘለዓለሙ፤

፳፮፤ ወይፌኑ፡ብርሃኖ፡ወየሐውሩ፤
ብርሃን : ረድኤቱን : ይሰድላቸዋል ፤
በብርሃን : ረድኤቱ : ጸንተው ፤
ይኖራሉ፤



፳፯፤ ወከዋክብትኒ : ያበርሁ : በጊዜ
ሆሙ፤
ከዋክብቱም : በጊዜያቸው : ጊዜ :
ያበራሉ፤

ወይትፌሥሑ፤
ደስ፡ይላቸዋል፤

፳፰፤ ወይጼውዖሙ፤
ይጠራቸዋል ፤ ሔልሜልሜሌክ ፤
ናርኤር፡ምልኤል፡እያለ፤

ወይብሉ፡ውእቱ፡አምላክነ፡መጸእነ፤
ፈጣሪያችን : እርሱ : ነው ፤ መጣን :
ይላሉ፤

እስመ፡አልቦ፡ባዕድ፡ዘይመስል፡ኪያሁ፤
እርሱን : የሚመስል : ሌላ : ፈጣሪ :
የለምና፤

፳፱፤ ውእቱ : ረከባ : ለኵላ : ፍኖተ :
ጥበብ፤
ሕገ፡ልቡናን፡የሠራት፡እርሱ፡ነው፤

ወወሀቦ፡ለያዕቆብ፡ቍልዔሁ፤
ለወዳጁ : ለያዕቆብ : ልትሆን :
የሠራት፡እርሱ፡ነው፤

ወለእስራኤል፡ፍቁሩ፤
ለወዳጁ : ለእስራኤልም : ልትሆን :
የሠራት፡እርሱ፡ነው፤

፴፤ ወእምዝ፡አስተርአየ፡ውስተ፡ምድር፤
ከዚህ፡በኋላ፡በደብረ፡ሲና፡ተገለጠ፤

ወኮነ፡ከመ፡ሰብእ፤
በሰው : አምሳል : በደብረ : ሲና :
በረድኤት : ታየ : ተገለጠ፤ አንድም :
ውእቱ : ረከባ : ለኵላ : ሕግ : መጽሐ
ፋዊን፡የሠራት፡እርሱ፡ነው፤ወወሀቦ፡
ለያዕቆብ : ለወዳጁ : ለያዕቆብ :
ልትሆን፡ወለእስራኤል፡ለወዳጁ፡ለእ
ስራኤልም፡ልትሆን፡የሠራት፡እርሱ፡
ነው፤ ወእምዝ : አስተርአየ : ውስተ :
ምድር : ወኮነ : ከመ : ሰብእ : ከዚህ :
በኋላ፡ሰው፡ሁኖ፡ሥጋ፡ለብሶ፡በዚህ፡
ዓለም፡ተገለጠ።

## ምዕራፍ : ፬ ፤

፩፤ ዝ፡ውእቱ፡መጽሐፈ፡ትእዛዙ፡ለእግ
ዚአብሔር፤
የእግዚአብሔር፡ትእዛዝ፡የተጻፈበት፡
የመጽሐፉ፡ትእዛዝ፡ይህ፡ነው፤

ወየሐይዉ፡ዘለዓለም፤
ለዘለዓለሙ፡በሕይወት፡ይኖራሉ፤

ወኵሎሙ፡እለ፡የዐቅብዋ፡የሐይዉ፤
ሕግን : የሚጠብቋት : ሰዎች : ሁሉ :
በሕይወት፡ይኖራሉ፤

ወእለሰ፡የሐድግዋ፡ይመውቱ፤
የሚተውዋት፡ሰዎች፡ግን፡ይሞታሉ፡
ይጠፋሉ፤

፪፤ ተመየጥ፡ያዕቆብ፡ወአኀዝ፤
ያዕቆብ : በአምልኮት : ተመልሰህ :
ሕጉን፡ያዝ፤

ወሑር፡በብርሃና፤
በሥርዓቷ፡ጸንተህ፡ኑር፤

፫፤ ወኢተሀብ፡ለባዕድ፡ክብረከ፤
ክብርህን፤ ባለፀግነትህን ፤ ለባዕድ :
ለአሕዛብ፤ለባዕድ፡ለጣዖት፡አትስጥ፤

ዘይኄይሰከ፡ለካልዕ፡ሕዝብ፤
ከሌላ : ወገን : የሚሻልህ : የሚበልጥ :
ባለፀግነትህን : ለባዕድ : ለጣዖት :
አትስጥ፤

፬፤ ብፁዓን፡ንሕነ፡እስራኤል፤
እኛ : እስራኤል : ንዑዳን : ክቡራን :
ን፡ይላሉ፤

www.ethiopianorthodox.org

እስመ፡ተአውቀ፡ምሕረቱ፡ለእግዚአብሔር፡
አምላክነ፡ላዕሌነ፡
የፈጣሪያችን ፡ የእግዚአብሔር ፡
ቸርነቱ፡በእኛ፡ላይ፡ታውቋልና፤

፭፤ ተአመኑ፡ሕዝብየ፡
ወገኖቼ፡እመኑ፡

ወተዘከሩ፡እስራኤል፡
እስራኤልም ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብ
ሔርን፡አስቡ፤

፮፤ ተሣየጥኩክሙ ፡ ለሕዝብየ ፡ ወአኮ ፡
ለኃጕል፡ዳዕሙ፡
ለጥፋት ፡ ብቻ ፡ ያይደለ ፡ ለወገንነት ፡
መረጥኋችሁ፤

እስመ፡አምአዕክምዎ፡ለእግዚአብሔር፡
እግዚአብሔርን፡አሳዝናችሁታልና፤

ገባዕክሙ፡ለፀርክሙ፡
ገባዕክሙን፡አስጠብቅ፤

፯፤ ወወሐክምዎ፡ለፈጣሪክሙ፡
ፈጣሪያችሁን፡አውካችሁታልና፤

ወሦዕክሙ ፡ ለአጋንንት ፡ ወአኮ ፡ ለእግዚአ
ብሔር፡
ለእግዚአብሔር፡ያይደለ፡ለአጋንንት፡
ሠውታችኋልና፤

፰፤ ወረሣዕክምዎ ፡ ለአምላክክሙ፡ዘሐ
ፀነክሙ፡ለዓለም፡
ለዘለዓለሙ ፡ ያሳደጋችሁ ፡ ፈጣሪያ
ችሁን፡ዘንግታችሁታልና፤

ወአተከዝክምዋ ፡ ለሐፃኒትክሙ ፡ ኢየሩ
ሳሌም፡
ሞግዚታችሁ፡ኢየሩሳሌምን፡አሳዝና
ችኋታልና፤

፱፤ ሶበ ፡ ርእየት ፡ መቅሠፍተ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ዘመጽአክሙ፡

መቅሠፍት ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ አሳዝናችኋ
ታልና፤

ገባዕክሙ፡ለፀርክሙ፡
በጠላቶቻችሁ ፡ እጅ ፡ ወደቃችሁ ፡
ብለህ፡እሠር፤

ስምዑ፡ፈላስያነ፡ጽዮን፡
ከጽዮን ፡ ተማርካችሁ ፡ የመጣችሁ ፡
እስራኤል፡ስሙ፤

እስመ ፡ አምጽአ ፡ ሊተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላሃ፡
ዓቢየ፡
እግዚአብሔር ፡ ጽኑ ፡ ልቅሶ ፡ አምጥቶ
ብኛልና፤

፲፤ ሶበ ፡ ርኢኩ ፡ ተዴውዎ ፡ አዋልድየ ፡
ወደቂቅየ፡
የሴቶች ፡ ልጆቼንና ፡ የወንዶች ፡
ልጆቼን፡ምርኮ፡በአየሁ፡ጊዜ፤

፲፩፤ ተአመኒ፡ኢየሩሳሌም፡
ማኅደረ፡እግዚአብሔር፡ያለሽ፡ኢየሩ
ሳሌም፡ደስ፡እንዲልሽ፡እመኚ፤

ያስተፌሥሐኪ፡ዘሰመየኪ፡
ኢየሩሳሌም ፡ ያለሽ ፡ እግዚአብሔር ፡
ደስ፡ያሰኝሻል፤

፲፪፤ ወየኀሥሩ፡እለ፡ሣቀዩኪ፡
መከራ ፡ ያፀኑብሽ ፡ ሰዎች ፡ ይጐሠ
ቍላሉ፤

ወእለ፡ይትፌሥሑ፡በድቀትኪ፡
በአንቺ ፡ ጥፋት ፡ ደስ ፡ የሚላቸው ፡
ሁሉ፡ይጠፋሉ፤

፲፫፤ ወየኀሥራ ፡ አህጉር ፡ እለ ፡ ቀነያ ፡
ደቂቀኪ፡
ልጆችሽን፡የ



ወእለ፡ተመጠዉ፡ውሉደኪ፡
ልጆችሽን ፡ የማረኩ ፡ ሰዎች ፡ ይጐሰ
ቍላሉ፤

፲፬፤ ነጽሪ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መንገለ ፡
ጽባሕ፡
ኢየሩሳሌም፡ወደ፡ምሥራቅ፡ዙረሽ፡
ተመልከቺ፤

ወርእዪ ፡ ፍሥሓ ፡ ዘመጽአ ፡ ለኪ ፡ እምኀበ ፡
እግዚአብሔር፡አምላክኪ፡
ከፈጣሪሽ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡
ታዝዞ ፡ የመጣልሽን ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡
እዪ፤

፲፭፤ ናሁ፡መጽኡ፡ደቂቅኪ፡
እነሆ፡ልጆችሽ፡አንድ፡ሁነው፡መጡ፤

ወተጋብኡ፡እለ፡ፈነዉኪ፡እምጽባሕ፡እስከ፡
ዓረብ፡
ከምሥራቅ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ አስማ
ርከሽ ፡ የሰደድሻቸው ፡ ልጆችሽ ፡
ተሰበሰቡ፤

በቃሉ፡ለቅዱስ፡
በጌታ፡ቃል፡

ወይትፌሥሑ፡በስብሐተ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር ፡ በሚያደርገው ፡ በተአ
ምራቱ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡ (በጌትነቱ ፡
ብትልም)።

## ምዕራፍ ፡ ፭ ፤

፩፤ አዕትቲ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አልባሰ ፡
ላህኪ፡ወሕማምኪ፡
ኢየሩሳሌም፡የኀዘንሽን፡የመከራሽን፡
ልብስ፡አርቂ፤

ወልበሲ ፡ ትርሲተ ፡ ክብርኪ ፡ ዘእምኀበ ፡ እግ
ዚአብሔር፡ለዓለም፡

ታዝዞ ፡ የማመጣልሽ ፡ የምትከበረ

በትን፡ሽልማትሽን፡ልበሺ፤

፪፤ ወተአጸፊ፡አጽፈ፡ጽድቅ፡ዘእምኀበ፡
እግዚአብሔር፡
ከእግዚአብሔር፡ዘንድ፡ታዝዞ፡የሚደ
ረግልሽ ፡ የምትከበሪበትን ፡ መጐና
ጸፊያ፡ተጐናጸፊ፤

ወተቀጸሊ፡ቀጸላኪ፡ውስተ፡ርእስኪ፡
ዘውድሽን፡በራስሽ፡ድፊ፤

በስብሐቲሁ፡ቅዱስ፡
ጽኑ፡ክቡር፡ልዩ፡በሚሆን፡በጌትነቱ፤

፫፤ እስመ፡እግዚአብሔር፡ያርኢ፡ለኵሉ፡
ዘታሕተ፡ሰማይ፡ብርሃንኪ፡
እግዚአብሔር ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡
ላሉት ፡ ሁሉ ፡ ብርሃን ፡ ረድኤትሽን ፡
ያሳያልና፤

፬፤ወይሰመይ፡ስምኪ፡ለዓለም፡በኀበ፡እግ
ዚአብሔር፡
ለዘለዓለሙ፡በእግዚአብሔር፡ዘንድ፡
ስምሽ፡ይጠራል፤

ጽድቅ፡
በዓልተ፡ጽድቅ፡ይባላል፤

ወሰላም፡
በዓልተ፡ሰላም፡ይባላል፤

ወክብር፡
በዓልተ፡ክብር፡ይባላል፤

ወፍርሀተ፡እግዚአብሔር፡
በዓልተ ፡ ፍርሀተ ፡ እግዚአብሔር ፡
ይባላል፤

፭፤ተንሥኢ፡ኢየሩሳሌም፡
ኢየሩሳሌም፡ተነሺ፤

ወቁሚ፡መልዕልተ፡
በላይ፡ቁሚ፤

ጽሪ፡መንገለ፡ጽባሕ፤
ሽ፡ምሥራቅ፡ተመልከቺ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወርእዪ፡ከመ፡ተጋብኡ፡ደቂቅኪ፡እምነበ፡ምዕራበ፡ፀሐይ፡እስከነ፡ጽባሕ፡

ከፀሐይ ፡ መግቢያ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፀሐይ ፡ መውጫ ፡ ድረስ ፡ ልጆችሽ ፡ እንደ፡ተሰበሰቡ፡እዩ፤

በቃሉ፡ለቅዱስ፡

በጌታ፡ቃል፤

ወይትፌሥሑ፡በዝክረ፡እግዚአብሔር፡

አምልኮተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማሰብ፡ደስ፡ይላችኋል፤

፮፡ወወጽኡ፡እምኀቤኪ፡

ልጆችሽ፡ከአንቺ፡ተለይተው፡ወጡ፤

ወወሰድዎሙ፡ፀሮሙ፡በእግሮሙ፡

ጠላቶቻቸው ፡ በእግራቸው ፡ ማርከው፡ወሰዷቸው፤

ወያመጽኦሙ፡እግዚአብሔር፡ኀቤኪ፡

እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ ያመጣቸዋል፤

እንዘ፡ይፀውርዎሙ፡በክብር፡ከመ፡መንበረ፡ንጉሥ፡

እንደ፡ንጉሥ፡ዙፋን፡አንሣ፡አንሣ፡እሽኮኮ፡እየተሸከሙ፡ያመጧቸዋል፤

፯፡ ወአዘዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይትሐታ ፡ ኵሉ፡አድባር፡ነዋሓት፡

እግዚአብሔር ፡ ረጃጅሞች ፡ ተራራዎች፡ይዋረዱ፡ዘንድ፡አዘዘ፡ማለት፡ነገሥታቱ፡ይጠፉ፡ዘንድ፡አዘዘ፤

ወይምላዕ፡ኵሉ፡ማዕምቅ፡

ጕድጓዳው ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ ይሞላ ፤

ወይዕሪ፡ምድር፡

ምድሩ፡ሁሉ፡የተካከለ፡ይሆን፡ዘንድ፤

ከመ ፡ ይሑር ፡ እስራኤል ፡ መጽያሕተ ፡ በስብሐተ፡እግዚአብሔር፡

እስራኤል ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚያደርገው ፡ በተአምራቱ ፡ (በጌትነቱ) ፡ ብትልም ፡ ጥርጊያውን ፡ ጐዳና ፡ ይዞ ፡ ይሔድ፡ዘንድ፤

፰፡ወይጼልሎሙ፡ኵሉ፡ዖም፡

ታላላቁ፡ዛፍ፡ሁሉ፡እስራኤልን፡ይጋርዳቸዋል፤

ወኵሉ፡ዕፅ፡ሠናየ፡መዓዛ፡ለእስራኤል፡

በጎ፡መዓዛ፡ያለው፡ጥቃቅኑም፡ዛፍ፡ሁሉ፡ይጋርዳቸዋል፤አንድም፡ወይጼልሎሙ፡ኵሉ፡ዖም፡ጥቃቅኑ፡ዛፍ፡ሁሉ፡ይጋርዳቸዋል፡ወኵሉ፡ዕፅ፡በጎ፡ረድኤት፡ይደረግላቸዋል፤

በትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ እስራኤል፡

በእስራኤል፡ፈጣሪ፡በእግዚአብሔር፡ትዕዛዝ፤

በፍሥሓ፡

በተድላ፡በደስታ፤

ወበብርሃነ፡ስብሐቲሁ፡

በጌትነቱ፡ብርሃን፡ረድኤት፤

ወበምሕረቱ፡

በቸርነቱ፤

ወበጽድቁ፡

በይቅርታው...



## ሰቆቃወ ፡ ኤርምያስ ፤
## ምዕራፍ፡፩፡
## ጉባዔ፤

ወእምዝ፡እምድኅረ፡ዼወውዎ፡ለኤርምያስ፤

ኤርምያስን ፡ ከማረኩት ፡ በኋላ ፡ በቤሩት ፡ አፋፍ ፡ ቁሞ ፡ የተናገረው ፡ ልቅሶ ፡ ይህ ፡ ነው፤ አንድም ፡ በማረኩት፡ ጊዜ ፡ የተናገረው ፡ ልቅሶ፤ አንድም ፡ እምቅድመ ፡ ይዼውውዎ ፡ ይላል፡ ሳይማርኩት ፡ ተከበው ፡ ሳሉ ፡ የተናገረው ፡ ልቅሶ ፤ አንድም ፡ ያለቀሰው፡ልቅሶ፡ይህ፡ነው፤

ወለኢየሩሳሌምኒ፡አማሰንዋ፡

ኢየሩሳሌምንም ፡ ሳያጠፏት ፤ አንድም ፡ ባጠፏት ፡ ጊዜ ፤ አንድም ፡ ካጠፏት ፡ በኋላ ፡ የተናገረው ፡ ልቅሶ ፡ ይህ፡ነው፤

ነበረ፡ኤርምያስኒ፡ይበኪ፤

ኤርምያስ፡ሲያለቅስ፡ኖረ፤

ወአስቆቀወ፡ዘከመዝ፡ሰቆቃወ፡ላዕለ፡ኢየሩሳሌም፤

በኢየሩሳሌም፡ላይ፡እንደእዚህ፡ያለ፡ልቅሶን፡አለቀሰ፤

፩፡አሌፍ፤

አሐዱ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤ ይህን፡አሌፋት፡ለኄኖስ፡በጸፍጸፈ፡ሰማይ፡አሳይቶት፡ጽፎታል፤ ከዚህ፡አስቀድሞ፡የአቤል፡ደም፡ያጥፋን፤ እያሉ፡ሲምሉ፡ነበር፤በዕሩቅ፡ብእሲ፡ደም ፡ መማል ፡ አይገባም ፡ ብሎ ፡ ወውእቱ፡ዘአኀዘ፡ይጸውእ፡ስመ፡እግ...

አምሳል ፡ ኋላም ፡ ነቢያት ፡ ግናያት ፡ አድርሰው ፡ ያሥሩበት ፡ ነበር ፤ ዛሬ ፡ እኛ፡ በአቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ጸሎታችንን ፡ እንድናሥር፤ ዳዊትም ፡ አግብቶ፡ ተናግሮታል፤ ኤርምያስ ፡ አራት፡ጊዜ፡መላልሶ፡ተናግሮታል፤

እፎ ፡ ነበረት ፡ ባሕቲታ ፡ ሀገር ፡ እንተ ፡ ምልዕት፡ሕዝበ፤

ሰው ፡ መልቶባት ፡ ትኖር ፡ የነበረች ፡ ሀገር፡እንደምን፡ብቻዋን፡ቀረች፤

ወኮነት፡መበለተ፤

ከሰው፡ከእንስሳ፡ተለይታ፡እንደምን፡ድኃ፡ሆነች፤አንድም፡አንድ፡እግዚአብሔርን ፡ አላመልክ ፡ ብላ ፡ ብዙ ፡ ጣዖታትን፡አምልካ፡እንደምን፡ድኃ፡ሆነች፤

እንተ፡ትኴንን፡አሕዛበ፤

ብዙ፡አሕዛብን፡ትገዛ፡የነበረች፤

ወትኴንን፡በሐውርተ፡

ሀገሩን፡ሁሉ፡ትገዛ፡የነበረች፤

ወገብአት፡ውስተ፡እደ፡ጸዋር፡

በጠላቷ ፡ እጅ ፡ እንዴት ፡ ወደቀች ፤ እንዴት፡ተያዘች፡ብትልም፤አንድም፡እግዚአ ፡ ኵሉ ፡ ጌታን ፡ አላመልክ ፡ ብላ፡ ኀሡር ፡ ጣዖትን ፡ አምልካ ፡ በጣዖት ፡ እጅ ፡ እንዴት ፡ ወደቀች ፤ አንድም ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ ጸዋር፡ ቢል ፡ ግብር ፡ ይሸከሙላታል ፤ አንድም ፡ ግብር ፡ ይሸከሙላት ፡ በነበሩ፡ ሰዎች ፡ እጅ፡ላይ፡እንዴት፡ወደቀች፤

፪፡ቤት፤

ባዕል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ቢያገናኙት ፡ አ... ማለት ፡ ነው ፤ የሚገናኝ ፡ የመጀ... ... የመጨረሻው ፡ ነው ፡

www.ethiopianorthodox.org